አዋጅ ቁጥር…/2010

**<u>የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ</u>**

ኢትዮጵያ ለስደተኞች መጠጊያና ከለላን የምትሰጥ እንዲሁም ሁኔታዎች በፈቀዱ ጊዜ ላሉባቸው ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኙ የምታበረታታ በመሆኑ፤

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ ጁላይ 28 ቀን 1951 በጄኔቫ የፀደቀው የስደተኞች ኮንቬንሽን፣ እ.ኤ.አ ጃንዋሪ31 ቀን 1967 በኒውዮርክ የፀደቀው የስደተኞች ፕሮቶኮልና እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር 10 ቀን 1969 በአዲስ አበባ የፀደቀው የአፍሪካ ስደተኞችን ችግር የተወሰኑ ገፅታዎች የሚገዛው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኮንቬንሽን አባል በመሆኗ፤

ከላይ በተጠቀሱ አለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ የተቀመጡ መብቶችን የያዘ፣ ለስደተኞች የተሻለ ከለላ የሚሰጥና ለችግሮቻቸው ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኙ የሚያስችል በዓለም አቀፍ መመዘኛዎች መሰረት የተቀረጸ የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፤

ስደተኞችን የሚመለከቱ በስራ ላይ ያሉ ሕጎች ተግባራዊ በሚደረጉበት ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት ሕጉን በማሻሻል እና በኢትዮጵያ የስደተኞች ከለላ አሰጣጥ ስራ ላይ ያለውን የተሻሻለ አሰራር እና ስኬታማ ተሞክሮዎችን በማካተት ወቅታዊ ሁኔታዎችን በሚያንጸባርቅ መልኩ የስደተኞች ጉዳይ ሕግን እንደገና ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>ጠቅላላ</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ------/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ "አገልግሎት" ማለት የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ነው፤

2/ "የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር" ማለት በኢትዮጵያ የሚገኘው የተባበሩትመንግስታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽህፈት ቤት ነው፤

3/ “የስደተኞች ኮንቬንሽን” ማለት እ.ኤ.አ ጁላይ 28 ቀን 1951 በጄኔቫ የፀደቀው የስደተኞችን ሁኔታ የሚመለከተው ኮንቬንሽን እና እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 31ቀን 1967 በኒውዮርክ የፀደቀው የስደተኞችን ሁኔታ የሚመለከተው ፕሮቶኮል ማለት ነው፤

4/ “የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የስደተኞች ኮንቬንሽን” ማለት እኤአ ሴፕቴምበር 10 ቀን 1969 በአዲስ አበባ የፀደቀውና የአፍሪካ ስደተኞችን ችግር የተወሰኑ ገፅታዎች የሚገዛው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኮንቬንሽን ማለት ነው፤

5/ “የዜግነት አገር” ማለት ስደተኛው ዜጋ የሆነበት አገር ነው፤

6/ “የቀድሞ መደበኛ መኖሪያ አገር” ማለት አንድ ሰው በቋሚነት ይኖርበትና ከለላ ያገኝበት የነበረ አገርነው፤

7/ “ስደተኛ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ወይም አንቀጽ 20 የተጠቀሰውን መስፈርት የሚያሟላ ሰው ነው፤

8/ “ጥገኝነት ጠያቂ” ማለት በድንበር ወይም በጠረፍ ላይ ሆኖ የስደተኝነት ዕውቅና

እንዲሰጠው የሚጠይቅ መሆኑን ያስታወቀ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው ሥልጣን ላለው አካል አመልክቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚጠብቅ ማንኛውም ሰው ወይም የሰዎች ቡድን ነው፤

9/ “የቤተሰብ አባል” ማለት፡-

ሀ) የስደተኛ ወይም የጥገኝነት ጠያቂ ባል ወይም ሚስት፣

ለ) ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ ያላገባ ስደተኛ ወይም

ጥገኝነት ጠያቂ ልጅ፣ወይም

ሐ) ስደተኛዉ ወይም ጥገኝነት ጠያቂው የመጣበትን አገር ባሕል፣ የቤተሰብ ትርጉም እንዲሁም እርስ በርስ ያላቸውን ጥገኝነት ግምት ውስጥ በማስገባት አገልግሎቱ በሚያደርገው ማጣራት እንደ ቤተሰብ የቆጠረው ሰው ነው፡፡

10/ “ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ” ማለት፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሠረት የስደተኝነት ዕውቅና ያገኘ፣ ወይም

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 መሠረት ስደተኛ ናቸው የተባሉ ሰዎች ቡድን አባል የሆነ ነው፡፡

11/ “የመታወቂያ ሰነድ” ማለት እውቅና ላገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በአገልግሎቱ የሚሰጥ እንደ የመታወቂያ ወረቀት፣ የመጓጓዣ ሰነድ፣ የይለፍ ወረቀት፣ የምዝገባ ማረጋገጫ ሰነድ፣ የልደት የምስክር ወረቀት እና ተመሳሳይ ማንነትን የሚገልጹ ሰነዶችን ይመለከታል፡፡

12/ በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተመለከተው አገላለጽ የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ጠቅላላ መርሆዎችና መስፈርቶች

### 3. ልዩነት አለማድረግ

ይህ አዋጅ በዘር፣ በኃይማኖት፣ በዜግነት፣ በአንድ የኅብረተሰብ ክፍል አባልነት፣ በፖለቲካ አስተሳሰብ ወይም በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### 4. የስደተኝነት መስፈርት

1/ ማንኛውም ሰው፣

ሀ/ በዘሩ፣ በኃይማኖቱ፣ በዜግነቱ፣ በአንድ የኅብረተሰብ ቡድን አባል በመሆኑ ወይም በፖለቲካ እምነቱ ምክንያት በእርግጥ ወይም በተጨባጭ ማሳደድ ወይም አደጋ ወይም እንግልት ወይም ስቃይ ይደርስብኛል ብሎ በመስጋቱ ምክንያት ከዜግነት አገሩ የተሰደደና በነዚሁ ክስተቶች ምክንያት የዜግነት አገሩን ጥበቃ ለማግኘት ያልቻለ ወይም ያልፈለገ እንደሆነ፣

ለ/ ዜግነት የሌለው ከሆነ በዘሩ፣ በኃይማኖቱ፣ በአንድ የተወሰነ ቡድን አባል በመሆኑ ወይም በፖለቲካ እምነቱ ምክንያት በእርግጥ ወይም ተጨባጭ ማሳደድ ወይም አደጋ ወይም እንግልትና ስቃይ ይደርስብኛል ብሎ በመስጋት ከቀድሞ መደበኛ የመኖሪያ ሥፍራው ለቆ የተሰደደ እና መመለስ ያልቻለ ወይም ያልፈለገ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ/ በውጭ ወረራ፣ በግዛት መያዝ፣ በውጭ አገዛዝ፣ የትውልድ ወይም የዜግነት አገሩን ህዝባዊ ሥርዓት በከፊልም ሆነ በሙሉ የሚያናጋ ከባድ ክስተት ምክንያት ከትውልድ ወይም ከዜግነት አገሩ ውጭ ጥገኝነት ለመጠየቅ ሲል መደበኛ መኖሪያ ሥፍራውን ለመልቀቅየተገደደ እንደሆነ፤

እንደ ስደተኛ ይቆጠራል፡፡

2/ አንድ ሰው ከአንድ በላይ ዜግነት ካለው ከእነዚህ አገሮች በአንዱ የሚሰጠውን ከለላ እርግጠኛ ወይም ተጨባጭ ስጋት ሳይኖረው ያለበቂ ምክንያት ያልተጠቀመ ከሆነ የዜግነት አገሩን ጥበቃ እንዳላገኘ አይቆጠርም፡፡

## 5. ከአገር መውጣት በኂላ በሚፈጠሩ ሁኔታዎች ስለሚሰጥ የስደተኝነት ዕውቅና

ማንኛዉም ሰውከዜግነት ወይም ከቀድሞ መኖርያ አገሩ ከወጣ በኂላበዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) ፣ (ለ) ወይም (ሐ) የተጠቀሱ ሁኔታዎች ሲከሰቱ እንደስደተኛ ይቆጠራል፡፡

## 6. እንደስደተኛ ስላለመቆጠር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 እና 5 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ሰው፡-

1/ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ እንደተደነገገው በሰላምና በስብዕና ላይ ወንጀል ወይም የጦርነት ወንጀል ስለመፈፀሙ፤

2/ ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ከፖለቲካ ወንጀል ውጭ ሌላ ከባድ ወንጀል ስለመፈፀሙ፤

3/ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ወይም የአፍሪካ ህብረት ቻርተር ውስጥ የተካተቱ ዓላማዎችንና መርሆዎችን በመጣስ ጥፋተኛ ስለመሆኑ፤

አሳማኝ ምክንያቶች የተገኙ እንደሆነ እንደስደተኛ አይቆጠርም፡፡

## 7. የስደተኝነት ዕውቅናን ስለመሠረዝ እና መሻር

1/ አገልግሎቱ፡-

ሀ) የስደተኝነት ዕውቅና የተሰጠውን ሰው የስደተኝነት ውሳኔ ሲሰጠው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 የተቀመጡትን የስደተኛነት መስፈርቶች ባለማሟላቱ ምክንያት እንደስደተኛ መቆጠር ያልነበረበት ከሆነ፣ ወይም

ለ) የስደተኝነት ዕውቅና የተሰጠውን ሰው የስደተኝነት ዕውቅና ውሳኔ ሲሰጠው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተካተቱት እንደስደተኛ የማያስቆጥሩ የስደተኝነት መስፈርቶች ምክንያት እንደስደተኛ መቆጠር ያልነበረበት ከሆነ፣

የስደተኝነት እውቅናውን ሊሰርዝ ይችላል፡፡

2/ የስደተኝነት ዕውቅና የተሰጠው ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (3) ስር የተጠቀሱት እንደስደተኛ እንዳይቆጠር የሚያደርጉ መስፈርቶች ዕውቅናውን ካገኘ በኂላ ተግባራዊ የሚሆኑበት ከሆነ አገልግሎቱ የስደተኝነት ዕውቅናውን ሊሽር ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የስደተኝነት ዕውቅና ከመሰረዙ ወይም ከመሻሩ በፊት አገልግሎቱ ለስደተኛው ስለሁኔታው በጽሁፍ ሊያስታውቀውና ጉዳዩን እንዲያስረዳ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

4/ የስደተኝነት ዕውቅናን የማንሳት ወይም የመሻር ውሳኔ ውሳኔው በተላለፈበት ሰው የቤተሰብ አባላት ላይም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም የቤተሰብ አባሉ በዚህ አዋጅ መሠረት በተናጥል የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው ማመልከቻ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ መሰረት አገልግሎቱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ስደተኛ ውሳኔውን በጽሁፍ በሰማ በስድሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

6/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ቢኖርም ይግባኝ ባዩ አሳማኝ ምክንያት ካቀረበ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ከስድሳ ቀናት በኋላ የቀረበን የይግባኝ ማመልከቻ ሊሰማ ይችላል፡፡

## 8. <u>እንደስደተኛ መቆጠር ስለሚያበቃበት ሁኔታ</u>

1/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በራሱ ፍላጎት በዜግነት አገሩ በሚሰጥ ጥበቃ መልሶ ተጠቃሚ የሆነ እንደሆነ፤

ለ) ዜግነቱን አጥቶ የነበረ ከሆነ በፈቃደኝነት መልሶ ካገኘ፤

ሐ) የሚደርስበትን ማሳደድ በመፍራት ለቆ በወጣው አገር ወይም በቋሚነት በሚኖርበት አገር ውስጥ ራሱን መልሶ ያቋቋመ እንደሆነ፤

መ) የኢትዮጵያ ወይም የሌላ አገር ዜግነት አግኝቶ በዚሁ በአዲሱ የዜግነት አገሩ በሚሰጥ ከለላ ተጠቃሚ የሆነ እንደሆነ፤ወይም

ሠ) በስደተኝነት ዕውቅና እንዲያገኝ ምክንያት የነበሩ ሁኔታዎች የቀሩ ወይም የተለወጡ ሆነው በዜግነት አገሩ የሚሰጠውን ከለላ ባለመጠቀም አቋሙ የቀጠለ እንደሆነ፤ወይም ዜግነቱን አጥቶ ከሆነ ወደ ቀድሞ መደበኛ መኖሪያ አገሩ አልመለስም ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የሌለ እንደሆነ፤

እንደስደተኛ መቆጠሩ ቀሪ ይሆናል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 4 ስር በተገለጹ ምክንያቶች በዜግነት አገሩ ወይም በቀድሞ መደበኛ መኖሪያ አገሩ የሚሰጥ ከለላ ለመጠቀም ካለመፈለግ የሚመነጩ አስገዳጅ ምክንያቶችን ማቅረብ በሚችል ስደተኛ ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በአገልግሎቱ በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ስደተኛ ውሳኔውን በጽሁፍ በሰማ በስድሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የይግባኝ ማመልከቻውን ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ቢኖርም ይግባኝ ባዩ አሳማኝ ምክንያት ካቀረበ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ከስድሳ ቀናት በኋላ የቀረበን የይግባኝ አቤቱታ ሊመለከት ይችላል፡፡

## 9. <u>የሁኔታዎች መሠረታዊ ለውጥ</u>

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀፅ 1 (ሠ) የተመለከቱት መሠረታዊ ለውጦች በዚህ አዋጅ መሰረት የስደተኝነት ዕውቅና ባገኘው ሰው ወይም ሰዎች የዜግነት አገር ወይም የቀድሞ መደበኛ መኖሪያ ቦታ መከሰቱ ከታመነ አገልግሎቱ ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በመተባበር ለዚሁ ተግባር አፈፃፀም ሲባል የሚዘጋጅን ልዩ ሥነ-ሥርዓት መሠረት በማድረግ እንዲሁም በመጀመሪያ የስደተኝነት ዕውቅና ለመስጠት ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በተከሰተው ለውጥ ጠባይና በቆይታው ላይ ምርመራና ማጣራት እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

2/ ከዚሁ ምርመራና ማጣራት በኋላ አገልግሎቱ ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በመተባበር ለሰውየው ወይም ለቡድኑ አባላት የተሰጠው የስደተኛነት ዕውቅና ቀሪ የሚደረግ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በተመለከተ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚሰጥ ውሳኔ የስደተኝነት ዕዉቅና ቀሪ በሆነበት ስደተኛ ወይም በስደተኞቹ ላይ ስለሚያስከትለው ውጤት እንዲሁም እያንዳንዱ ስደተኛ ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳለው መግለጽ አለበት፡፡

## 10. <u>ተገዶ ስላለመመለስ</u>

1/ ማንኛውም ሰው ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ በመከልከሉ ወይም ከኢትዮጵያ ለቆ እንዲወጣ ወይም ወደመጣበት እንዲመለስ በመደረጉ ወይም በማናቸውም ሌላ እርምጃ ምክንያት፡-

ሀ) ዘሩን፣ ኃይማኖቱን፣ ዜግነቱን፣ የአንድ ማህበራዊ ቡድን አባልነቱን ወይም የፖለቲካ እምነቱን ምክንያት በማድረግ ማሳደድ፣ መሰቃየት ወይም መንገላታት ወደ ሚደርስበት አገር ወይም፣

ለ) በውጭ ወረራ፣ በግዛት መያዝ፣ በውጭ አገዛዝ ወይም የአገሪቱን ሕዝባዊ ሥርዓት ወይም ፀጥታ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በከባድ ሁኔታ በሚያናጋ ሁኔታ ህይወቱ፣ አካሉ፣ ስብዕናው ወይም ነፃነቱ አደጋ ላይ ወደሚወድቅበት አገር፣

እንዲመለስ ወይም በዚያው እንዲቆይ የሚያስገድደው ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ አይከለከልም ወይም ከኢትዮጵያ ለቆ እንዲወጣ ወይም ወደ መጣበት እንዲመለስ አይደረግም፡፡

2/ ለአገር ደህንነት አስጊ ለመሆኑ አሳማኝ ምክንያቶች የተገኙ ከሆነ ወይም ከባድ ወንጀል ፈፅሞ በፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ መሰረት ለኅብረተሰቡ አደገኛ ነው ተብሎ ጥፋተኛ የተባለ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ተጠቃሚ አይሆንም፡፡

3/ አገልግሎቱ ይህን አዋጅና ሌሎች ሕጎችን መሠረት በማድረግ አንድ ሰው ለአገር ደህንነት አስጊ ለመሆኑ ከባድ ምክንያቶች መኖራቸውን ያረጋግጣል፡፡

## 11. ከአገር ስለማስወጣት

1/ በብሔራዊ ፀጥታ ወይም በሕዝብ ሠላም ምክንያት ካልሆነ በስተቀር እውቅና ያገኘ ስደተኛ ከአገር እንዲወጣ አይደረግም፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከአገር የማስወጣት ትዕዛዝ የሚሰጠው በአገልግሎቱ ነው፡ ፡አገልግሎቱ ትዕዛዙን የሚሰጠው የሕግ ስርዓት በመከተልና ስደተኛው በጉዳዩ ላይ ምላሹን አቅርቦ እንዲያስረዳ በመፍቀድ ይሆናል፡፡

3/ ማንኛውም የማስወጣት ትዕዛዝ ከነምክንያቱ ለስደተኛው በፅሁፍ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

4/ ከአገር እንዲወጣ በታዘዘ ስደተኛ ጥያቄ ሲቀርብ የማስወጣቱ ትዕዛዝ ስደተኛው በሌላ አገር በሕጋዊነት ለመኖር እንዲፈቀድለት ለማመልከት እንዲያስችለው በቂ ለሆነ ጊዜ ሊዘገይ ይችላል፡፡

## 12. ለጊዜው በእስር ስለማቆየት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት ከአገር እንዲወጣ የታዘዘ ስደተኛ ከአገር እስኪወጣ ድረስ የማስወጣት ትዕዛዙን ለማስፈጸም አስፈላጊ ከሆነ ወይም የሀገሪቱን ደህንነት ለማስጠበቅ ወይም የሕዝቡን ሰላም ለማስከበር አገልግሎቱ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ለጊዜው ሊታሰር ወይም በማረፍያ እንዲቆይ ሊደረግይችላል፡፡

## 13. የቤተሰብ አንድነት

1/ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የጥገኝነት ጠያቂው የቤተሰብ አባል የጥገኝነት ጥያቄው ጉዳይ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመግባትና ለመቆየት ይፈቀድለታል፡፡

2/ ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ቤተሰብ አባል የሆነ ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ወደ ኢትዮጵያ መግባትና መቆየት ይፈቀድለታል፡፡

3/ የጥገኝነት ጠያቂው ወይም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛው የቤተሰብ አባላት ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉበት ጊዜ ጥገኝነት ጠያቂው ወይም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛው ያለው መብት ተጠቃሚ እና ለግዴታዎቹም ተገዢ ናቸው፡፡

4/ ይህ አንቀጽ የጥገኝነት ጠያቂ ወይም እውቅና ያገኘ ስደተኛ ቤተሰብ አባል ኢትዮጵያ ውስጥ ባለ ጊዜ በዚህ አዋጅ መሠረት የስደተኝነት እውቅና እንዲሰጠው ማመልከቻ ከማቅረብ አይከለክለውም፡፡

5/ ኢትዮጵያ ውስጥ ካለ የቤተሰብ አባል ጋር አንድ ላይ የመሆን ጥያቄ በጥገኝነት ጠያቂ ወይም ዕውቅና ባገኘ ስደተኛ በሚቀርብበት ጊዜ አገልግሎቱ የቤተሰቡ አባላት አንድ ላይ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የስደተኝነት ሁኔታ አወሳሰን ሥነ-ሥርዓት

### 14. የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጥ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በድንበር ላይ ሆኖ ወይም በማንኛውም መግቢያ በር በሕጋዊም ሆነ ሕጋዊ ባልሆነ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ የገባ እና ኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት በስደተኝነት ለመቆየት የፈለገ ማንኛውም ሰው በሰላሳ ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ለሚገኝ የአገልግሎቱ ጽህፈት ቤት ወይም ቅርንጫፍ ወይም ፖሊስ ጣቢያ ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡

2/ አገልግሎቱ በአመልካቹ ጥያቄ መሰረት ማመልከቻው ዘግይቶ የቀረበው አሳማኝ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካረጋገጠ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ጊዜ ካለፈ በኂላ እንዲያመለክት ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ማመልከቻ የተቀበለ ፖሊስ ጣቢያ ማመልከቻውን ወዲያውኑ ለአገልግሎቱ ማስተላለፍ አለበት፡፡

4/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ማመልከቻውን በአካል ማቅረብ ያልቻለ ጥገኝነት ጠያቂ በሌላ ሰው አማካኝነት እንዲያቀርብ አገልግሎቱ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

5/ የቤተሰብ አባላት በግላቸው ማመልከቻ ማቅረብ ካልፈለጉ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) መሰረት የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጥ የቀረበ ማመልከቻ በሁሉም የአመልካቹ የቤተሰብ አባላት እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡ ከወላጅ ወይም ከአሳዳሪ የተለየ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ በራሱ ወይም በአሳዳሪው አማካይነት የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

6/ አመልካቹ አገልግሎቱ የሚያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት የሰጠው መግለጫ እውነት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

7/ ማንኛውም ጥገኝነት ጠያቂ የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው ማመልከቻ ካቀረበ በኂላ በማንኛውም ጊዜ ሂደቱን ከተወ አገልግሎቱ ማመልከቻውን የማጣራት ሂደት ያቋርጣል፡፡

8/ የስደተኝነት ዕውቅና ለማግኘት ባመለከተ ወይም በማመልከት ላይ በሚገኝ ሰው ላይ አገር ውስጥ በመግባቱ ወይም በአገር ውስጥ በመገኘቱ ምክንያት የወንጀል ክስ አይቀርብም፣ አይቀጥልም ወይም ቅጣት አይጣልም፡፡

## 15. <u>በአገልግሎቱ ስለሚሰጥ ውሳኔ</u>

1/ አገልግሎቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 መሰረት የሚቀርብ ማመልከቻን መርምሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ወይም 5 የተደነገገው መስፈርት መሟላቱን ሲያረጋግጥ ማመልከቻውን ከመዘገበበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ የስደተኝነት ዕውቅና ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2/ አገልግሎቱ የቀረበለትን ማመልከቻ ለመወሰን በሚመረምርበት ወቅት፤

ሀ) አስፈላጊው መረጃ በተለይም ስለዕውቅና አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት እና የስደተኞችና የጥገኝነት ጠያቂዎች መብቶችና ግዴታዎች በተመለከተ ለአመልካቹ በሚገባው ቋንቋ የተሰጠው መሆኑን፣

ለ) አመልካቹ ጉዳዩን አቅርቦ ለማስረዳት በቂ ጊዜ የተሰጠው መሆኑን፣

ሐ) ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ የማመልከቻ አቅራቢውን የፆታ ምርጫ ግምት ውስጥ በማስገባት ብቁ የሆነ አስተርጓሚ መመደቡን፣

መ) ማመልከቻው በሚመረመርበት ወቅት በብሔራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የስደተኞች ጉዳይ ሕጎች ላይ አስፈላጊው ዕውቀት ያለው፣ የጥገኝነት ጠያቂዎችን ልዩ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ማስገባት የሚችልና ከማመልከቻ አቅራቢው የፆታ ምርጫ ጋር የሚሄድ ብቁ ባለሙያ መመደቡን፣

ሠ) ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ የስደተኝነት ዕውቅና ማመልከቻ በሚመረምርበት እና በሚወስንበት ጊዜ በቀዳሚነት የልጁን መልካም አስተዳደግ እና ጥቅም መከበር ታሳቢ መደረጉን፣

ረ) የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር በታዛቢነት እንዲገኝ መጋበዙን፣

ማረጋገጥ አለበት፡፡

3/ አገልግሎቱ በስደተኝነት ማመልከቻ ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ እስከምክንያቱ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

4/ አገልግሎቱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔውን በሰማ በስድሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የይግባኝ ማመልከቻውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ቢኖርም ይግባኝ ባዩ አሳማኝ ምክንያት ካቀረበ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ከስድሳ ቀናት በኋላ የቀረበን ይግባኝ ሊሰማ ይችላል፡፡

## 16. <u>የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ስለመቋቋም</u>

አገልግሎቱ ከስደተኝነት እውቅና ጋር በተያያዘ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርብን ቅሬታ የሚመለከት የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ (ከዚህ በኋላ "ጉባኤ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

## 17. <u>የጉባዔው አባላት</u>

1/ ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

ሀ) የአገልግሎቱ ተወካይ ……………………………………ሰብሳቢ

ለ) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ ………………………አባል

ሐ) የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ተወካይ …………………አባል

መ) የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተወካይ………………………አባል

ሠ) የፌደራልና አርብቶ አደር ልማት
ጉዳዮች ሚኒስቴር ተወካይ...............................................አባል

2/ የተባበሩትመንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር በታዛቢነት እንዲሳተፍ በአገልግሎቱ ይጋበዛል፡፡

3/ አገልግሎቱ ለጉባዔው ፀሐፊ ይመድባል፡፡

4/ አገልግሎቱ የጉባዔው አባላት በአገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የስደተኞች ጉዳይ ሕጎች እንዲሁም በስደተኛ እውቅና አሰጣጥ ውሳኔ መርሆዎች፣ መስፈርቶችና ሥነ-ሥርዓቶች ላይ በቂ እውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

## 18. <u>የጉባዔው ስልጣንና ተግባር</u>

1/ ጉባኤው በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቀርብለትን ይግባኝ መርምሮ በዘጠና ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2/ ጉባዔው የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት፤

ሀ) አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን አቅርቦ ለማስረዳት በቂ ጊዜ የተሰጠው መሆኑን፣

ለ) ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ የአቤቱታ አቅራቢውን የፆታ ምርጫ ግምት ውስጥ በማስገባት ብቁ አስተርጓሚ መመደቡን፣

ሐ) ከወላጅ ወይም አሳዳሪ የተለየ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ጉዳይ በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ በቀዳሚነት የልጁን መልካም አስተዳደግ እና ጥቅም መከበር ታሳቢ መደረጉን፣

ማረጋገጥ አለበት፡፡

3/ ጉባዔው የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ መርምሮ የአገልግሎቱን ውሳኔ ለማጽናት፣ ለማሻሻል፣ ለመለወጥ ወይም ለመሻር ይችላል፡፡

4/ ጉባዔው የሚሰጠውን ውሳኔ ከነምክንያቱ ለአቤቱታ አቅራቢው በጽሑፍ እንዲያውቅ ያደርጋል፡፡

5/ የጉባዔው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፤ ሆኖም ጉባዔው የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለው ብሎ የሚያምን ወገን ውሳኔው በጽሁፍ በደረሰው በሰላሳ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

6/ ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት የሚወስን ውስጠ ደንብ ያወጣል፡፡

## 19. <u>ስለመዛግብትና ቃለ ጉባዔዎች አያያዝ</u>

የስደተኝነት ዕውቅናን ለማግኘት የቀረበ ማመልከቻን የሚመለከቱ መዛግብት እና ቃለ ጉባዔዎች የአመልካቹን ጥበቃና ደህንነት ለአደጋ እንዳያጋልጡ ሆነው በምስጢርና በአስተማማኝ ሁኔታ መጠበቅ አለባቸው፡፡

## 20. <u>የቡድን የስደተኝነት ዕውቅና ስለመስጠት</u>

1/ አገልግሎቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟሉ የአንድ የሰዎች ቡድን ስደተኞች ናቸው ብሎ ለመወሰን ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የቡድን ስደተኝነት ዕውቅና ሲሰጥ አገልግሎቱ ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በመመካከር ውሳኔው ላይ

ለመድረስ ምክንያት የሆኑ በጥገኝነት ጠያቂዎቹ የዜግነት አገር ወይም መደበኛ የመኖሪያ ሥፍራ የተፈጠሩ ክስተቶችን፣ የውሳኔው ተጠቃሚ ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶችን እንዲሁም ውሳኔው ተፈጻሚ የሚሆንበትን ጊዜ በመግለጽ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም አገልግሎቱ ውሳኔው ተፈጻሚ ከሚሆንበት የጊዜ ገደብ በፊት ከዜግነት ወይም ከመደበኛ የመኖሪያ አገራቸው የለቀቁ ጥገኝነት ጠያቂዎች የቡድን ስደተኝነት ዕውቅና ውሳኔው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

4/ አገልግሎቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት የቡድን ስደተኝነት ዕውቅና ለመስጠት ምክንያት የሆኑ ክስተቶች የቀሩ ወይም የተለወጡ መሆኑንና ተጨባጭ ስጋት የመሆናቸው ሁኔታ ማብቃቱን የጥገኝነት ጠያቂዎቹ የመነሻ አገር በተመለከተ የተገኘውን መረጃ ግምት ውስጥ በማስገባትና ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በመመካከር ሲያረጋግጥ የቡድን ስደተኝነት ዕውቅና ውሳኔ የመስጠት ሂደቱ ማብቃቱን በመግለጽመመሪያ ያወጣል፡፡

## ክፍል አራት
## የጥገኝነት ጠያቂዎች እና ዕውቅና ያገኙ
## ስደተኞች መብቶችና ግዴታዎች

### 21. አጠቃላይ መብቶችና ግዴታዎች

ማንኛውም ጥገኝነት ጠያቂ እና ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ፣

1/ በስደተኞችኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የስደተኞች ኮንቬንሽን እንዲሁምአግባብነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ሕጐች በተደነገጉ መብቶች ተጠቃሚ ይሆናል፤ግዴታዎችንያከብራል፡፡

2/ ከዚህ አዋጅ ዓላማዎችጋርእስካልተቃረነ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ በስራ ላይ ባሉ በማናቸውም ሕጎችና ድንጋጌዎች ይገዛል፡፡

### 22. ኢትዮጵያ ውስጥ የመቆየትመብት

1/ በዚህ አዋጅ መሠረት የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው ያመለከተ ማንኛውም ሰው አገልግሎቱ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ፣ ወይም ማመልከቻው ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ እንደሆነ የይግባኝ መብቱ እስኪያበቃ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆይ ይፈቀድለታል፡፡

2/ በዚህ አዋጅአንቀጽ 10 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው ያቀረበውን ማመልከቻ ከተወ፣ በአገልግሎቱ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ካላቀረበ ወይም ይግባኝ ሰሚ ጉባዔው የይግባኝ አቤቱታውን ካልተቀበለው አግባብነት ባላቸው የኢሚግሬሽን ሕጎች መሠረት ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ግለሰቡ ወደ ሌላአገር መግባት እንዲችል በቂ ለሆነ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆይ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

4/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ የመኖር መብት አለው፡፡

## 23. ትምህርት ስለማግኘት

1/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ የቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ዜጎችን ያክል ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

2/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ የአገሪቱ አቅም በሚፈቅደው መጠን እና በአገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ መሰረት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ የከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና፣ የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት እድል ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

3/ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ውጭ በሆኑ የትምህርት ዘርፎች ውስጥ በተለይም የትምህርት ተደራሽነት፣ የውጭ አገር የትምህርት የምስክር ወረቀቶች፣ ዲፕሎማዎች እና ዲግሪዎችን ዕውቅና የማግኘት፣ የትምህርት ክፍያ ስረዛ እና ነፃ የትምህርት ዕድሎችን ማግኘት በተመለከተ አግባብ ባላቸው ሕጐች መሰረት ለውጭ አገር ዜጐች የሚደረገው የተሻለውን ያህል ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

## 24. የጤና አግልግሎት ስለማግኘት

ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛና ጥገኝነት ጠያቂ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

## 25. የመስራት መብት

1/ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የቅጥር ስራን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለውጭ አገር ዜጎች ከተሰጡ መብቶች የተሻለውን ያህል ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

2/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት እንደ እርሻ፣ ኢንዱስትሪ፣ አነስተኛና ጥቃቅን፣ እደጥበባትና ንግድ የመሳሰሉ ዘርፎች ውስጥ በግል ለመሰማራትና የንግድ ማኅበሮችን ለማቋቋም ለውጭ አገር ዜጎች ከተሰጡ እጅግ የተሻለውን መብቶች ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

3/ ሥልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል የተረጋገጠ የትምህርት ማስረጃ ያለው ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ በሙያው ለመስራት ከፈለገ ለውጪ አገር ዜጎች በተፈቀዱ የስራ መስኮች ውስጥ ለውጭ አገር ዜጎች ከተሰጡ መብቶች እጅግ የተሻለውን ያህል ተጠቃሚ ይደረጋል፡፡

4/ የኢትዮጵያ መንግስትና አለም አቀፍ ህብረተሰብ በጋራ በሚቀርጿቸው ስደተኞችና ኢትዮጵያውያንን የሚጠቅሙ እንደ እርሻ፣ አካባቢ ጥበቃ፣ ኢንዱስትሪና አነስተኛና ጥቃቅን ዘርፎች የመሳሰሉ የገጠርና የከተማ ፕሮጀክቶች ላይ የሚሰሩ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች አብረዋቸው ከሚሰሩ የኢትዮጵያ ዜጎች ጋርተመሳሳይ አያያዝ ይደረጋል፡፡

5/ አገልግሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት በተገለጹ ፕሮጀክቶች ላይ እንዲሳተፍ ለተመረጠ ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ በየአምስት አመቱ የሚታደስ የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

6/ በስራ ላይ በተሰማሩ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች እና በኢትዮጵያ ዜጎች መካከል መድልኦ አይደረግም፡፡

7/ አግባብነት ያላቸው መብቶች እና ግዴታዎችን የሚደነግጉ የአገሪቱ ሕጉች በስራ ላይ በሚሰማሩ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

8/ አግባብነት ባላቸው ሕጎች የአገር ውስጥ የስራ ገበያን ለመከላከል በውጭ አገር ዜጎች ላይ የቅጥር ስራ መብትን አስመልክቶ የተጣሉ ክልከላዎች ከኢትዮጵያ ዜጋ ጋር ጋብቻ በፈጸመ ወይም አንድና ከአንድ በላይ የኢትዮጵያ ዜግነት የያዘ ልጅ ያለው ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

9/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በማናቸውም የሀገር መከላከያ፣ የሀገር ደኅንነት፣ ወይም በውጭ ጉዳይና መሰል የፖለቲካ የመንግስት መስሪያቤቶች በመደበኛነት ተቀጥሮ የመስራት መብት የለውም፡፡

## 26. የመደራጀት መብት

ከፖለቲካ ነፃ በሆኑ እና ለትርፍ ባልተቋቋሙ ማኀበራትእንዲሁም በሠራተኛ ማኀበራት የመደራጀት መብትን አስመልክቶ ለውጭ አገር ዜጎች ከተሰጡ መብቶች እጅግ የተሻለውን ያህል ዕውቅና ያገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

## 27. የመዘዋወር ነፃነት

1/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ለውጪ አገር ዜጎች በአጠቃላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ የሚሆኑ ሕጎች ተግባራዊ በማድረግ በመረጠው የአገሪቷ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከአገር የመውጣት ነጻነት አለው፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም አገልግሎቱ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሚኖሩባቸውን ቦታዎችና አካባቢዎች ሊያመቻች ይችላል፡፡ የሚያመቻቸው የመኖሪያ ቦታ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ከመጡበት የዜግነት ወይም የቀድሞ መደበኛ መኖሪያ አገር ተገቢው ርቀት እንዲኖረው በማድረግ መሆን አለበት፡፡

3/ አገልግሎቱ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ከቦታ ቦታ የመዘዋወር መብታቸውን እንዲጠቀሙ ለማስቻል ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይችላል፡፡

## 28. ንብረት የማፍራትና የማስተላለፍ መብት

1/ እዉቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረትን በባለቤትነት መያዝ እና ከዚህ ጋር የተያያዙ ሌሎች መብቶችን እንዲሁም ከንብረት ጋር የተያያዘ የኪራይና ሌሎች ውሎች ጋር የሚዛመዱ መብቶችን በሚመለከት ለውጭ አገር ዜጐች ከተሰጡ መብቶች እጅግ የተሻለውን ያህል ጥበቃ ይደረግታል፡፡

2/ እዉቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉ የአእምሮአዊ ንብረቶች ማለትም የፓተንት፣ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች፣ የንግድ ምልክት፣ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍና የመሳሰሉ መብቶችን በተመለከተ የኢትዮጵያ ዜጋ የሚያገኘውን መብት ያህል በተመሳሳይ ያገኛሉ፡፡

3/ ጥገኝነት ጠያቂዎች አግባብነት ባላቸው የጉምሩክ ሕጎች መሰረት ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ የተከለከሉ ወይም ገደብ የተጣለባቸው ዕቃዎችን በተመለከተ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ወደ አገር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገቡ ይዘውት የሚመጡትን ሃብትና ንብረት ያለቀረጥ እንዲያስገቡ ይፈቀድላቸዋል፡፡

4/ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት ከአገር እንዳይወጡ የተከለከሉ ወይም ገደብ የተጣለባቸው እቃዎችን በተመለከተ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ዕውቅና ያገኙስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች ወደ መጡበት አገር ሲመለሱ

ወይም ወደ ሶስተኛ አገርበሚወጡበት ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ይዘው የመጡት ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ያፈሩትን ሐብትና ንብረት ይዘው እንዲወጡ ይፈቀድላቸዋል፡፡

## 29. ፍትሕ የማግኘት መብት

1/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ ከዜጎች እኩል በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡

2/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር አማካኝነትና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሚሰጡ ነፃ የሕግ ምክርና የድጋፍ አገልግሎቶችን ሊያገኝ ይችላል፡፡

## 30. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ

1/ አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተቀመጡ ድንጋጌዎች የሚጠይቋቸውን መስፈርቶች በማሟላት በኢትዮጵያ መንግሥት ተቀባይነት ያለው ሕጋዊ የውጭ አገር ወይም ዓለም አቀፍ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የያዘ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በኢትዮጵያ ተመጣጣኝ ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊያመለክትና ሊሰጠው ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1)መሠረት ሕጋዊ የውጭ አገር ወይም ዓለም አቀፍ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የያዘ ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በኢትዮጵያ ተመጣጣኝ ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማግኘት እንዲችል ለመርዳትአስፈላጊውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና ለመውሰድ ፈቃደኛ ሆኖ ከተገኘ አግባብ ባላቸው ሕጎች የተቀመጡት መስፈርቶች ሊነሱለት ይችላሉ፡፡

3/ በሌላ ሕግ ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂአግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጐች የተቀመጡ መሥፈርቶችን በማሟላት በአገልግሎቱ የሚሰጥ ማንነቱን የሚገልጽ የመታወቂያ ሰነድ በመጠቀም የኢትዮጵያ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫፈቃድ ለማግኘት የማመልከት እና ተፈላጊውን መመዘኛ ካሟላ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የማግኘት መብት አለው፡፡

## 31. የመታወቂያ ወረቀት እና የጉዞ ሰነድ

1/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ማንነቱን የሚገልጽ የመታወቂያ ሰነድ ይሰጠዋል፡፡

2/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ከኢትዮጵያ ውጭ ጉዞ ለማድረግ ለአገልግሎቱ በጽሑፍ በማመልከት የጉዞ ሰነድ ማግኘት ይችላል፡፡

3/ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች የጉዞ ሰነድ ዝግጅት፣ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እና አሰጣጥ እንዲሁም ሌሎች ጠቃሚ ዝርዝሮች አግባብነት ባላቸው የኢሚግሬሽን ሕጎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ በተመለከተው መሠረት ይወሰናል፡፡

## 32. <u>የባንክ አገልግሎት ስለማግኘት</u>

ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በአገልግሎቱ የተሰጠውን መታወቂያ ሰነድ በመጠቀም የባንክ ሒሳብ ደብተር የመክፈት፣ ገንዘብ የማስቀመጥ፣ የማውጣት፣ የማስተላለፍና የመሳሰሉ የባንክ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አለው፡፡

## 33. <u>የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ስለማግኘት</u>

ማንኛውም እውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በአገልግሎቱ የተሰጠውን መታወቂያ ሰነድ በመጠቀም የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት የማግኘት መብት አለው፡፡

## 34. <u>ራሽን ስለማግኘት</u>

በአቅርቦት እጥረት ምክንያት በራሽን መልክ ምርቶች ለማህበረሰቡ በሚከፋፈሉበት ወቅት ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ከኢትዮጵያ ዜጎች ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

## 35. <u>የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ</u>

ማንኛውም ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ አግባብ ያላቸው የወሳኝ ኩነቶችን በተመለከተ የወጡ ሕጎች መሰረት የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አገልግሎት ከዜጎች እኩል የማግኘት መብት አለው፡፡

## 36. <u>ክፍያዎች</u>

1/ ማንኛውም አይነት ቀረጥ፣ ክፍያ ወይም ግብርን በተመለከተ በተመሳሳይ ሁኔታ ያሉየኢትዮጵያ ዜጎች ላይ ከሚጣለው መጠን በላይ ዕውቅና ባገኙ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች ላይ አይጣልም፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተደነገገው ቢኖርም አገልግሎቱ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች የመታወቂያ ሰነድ፣ የጉዞ ሰነድ፣ የመውጫ ቪዛና የመሳሰሉ አገልግሎቶች ያለ ክፍያ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

37. <u>ለጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች ስለሚደረግ ልዩ ጥበቃ</u>

አገልግሎቱ፡-

1/ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂ ሴቶች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉ መብቶችና ጥበቃዎች በተለይም ጾታን መሰረት ካደረገ ጥቃት ጥበቃ ማግኘታቸውን፣
2/ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂ ህጻናት አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉ መብቶችና ጥበቃዎች በተለይም ከጥቃት፣ ከእንግልት፣ ከብዝበዛና ከሕገወጥ ዝውውር ጥበቃ ማግኘታቸውን፣
3/ ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው ለጥቃት ለተጋለጡ ሌሎች እውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ፍላጎቶቻቸውን መሰረት ያደረገ እገዛ መደረጉን፣

ያረጋግጣል፡፡

**38.** <u>ዕውቅና ያገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ግዴታዎች</u>

1/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ ከአገልግሎቱ ጋር የመተባበር፣ በአገልግሎቱ አስፈላጊውን መረጃ ሲጠየቅ የመስጠትና በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ያሉ ማናቸውንም ሕጎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

2/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ የሚኖርበትን አካባቢ ባህል የማክበር እና ከአካባቢው የመልካም አኗኗርና የሕዝብ ሞራል ተቃራኒ ከሆኑ ተግባራት የመቆጠብ ግዴታ አለበት፡፡

3/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ ከባቢውን የመንከባከብ ኃላፊነት አለበት፡፡

**39.** <u>በፈቃደኝነት ወደ አገር ስለመመለስ</u>

1/ ማንኛውም ስደተኛ በራሱ ነጻና በመረጃ ላይ በተመሰረተ ፈቃድ ወደ ዜግነት አገሩ ወይም ወደ ቀድሞ መደበኛ መኖሪያ ቦታው ደህንነቱና ክብሩ ተጠብቆለት የመመለስ መብት አለው፡፡
2/ አገልግሎቱ ወደ አገራቸው ለመመለስ ለጠየቁ ስደተኞች ከስደተኞቹ መነሻ አገር፣ ከተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነርና ሌሎች አጋር ድርጅቶች

ጋር በመተባበር የሚቻለውን ያክል ድጋፍ በማድረግ ፈቃዳቸው፣ደህንነታቸውና ክብራቸው ተጠብቆ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ያመቻቻል፡፡

**40. <u>ከዜጎች ጋር ስለማዋሃድ</u>**

ለረጅም ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩ ስደተኞች ከአገሪቱ ዜጎች ጋር ተዋህደው ለመኖር ሲጠይቁ በቡድንም ይሁን በተናጥል ከዜጎች ጋር ተዋህደው የሚኖሩበትን ሁኔታ አገልግሎቱ ሊያመቻች ይችላል፡፡

**41. <u>ዜግነት ስለማግኘት</u>**

ዜግነትን በሚመለከቱ አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ ድንጋጌዎች የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም እውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ የኢትዮጵያን ዜግነት በሕግ ለማግኘት ማመልከት ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**42. <u>ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር ስለሚደረግ ትብብር</u>**

የኢትዮጵያ መንግስት የተባበሩትመንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር በስደተኞች ኮንቬንሽን አንቀጽ 35 መሰረት ኃላፊነቱን ለመወጣት እንዲችል ትብበር ያደርጋል፡፡

**43. <u>ምስጢር መጠበቅ</u>**

ይህን አዋጅ እንዲሁም በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎችን የሚያስፈፅም ማንኛውም ሰው በስራው ምክንያት የሚያገኘውን ከጥገኝነት ጠያቂ ወይም ከስደተኛ ጋር የተያያዘ ማንኛውም መረጃ በምስጢር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ በተለይም ከስደተኛው ወይም ከጥገኝነት ጠያቂው አገር ባለሥልጣናት ወይም ስቃይ አድርሰዋል ከተባሉ አካላት መረጃ አይሰበስብም፤ መረጃም አሳልፎ አይሰጥም፡፡

**44. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

1/ የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 409/1996 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

2/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 45. *የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች*

1/ በስራ ላይ በነበሩ ሕጎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች መሰረት የተከናወኑ ጉዳዮች ጸንተው ይቆያሉ፡፡

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ቢኖርም በአዋጅ ቁጥር 409/1996 መሰረት የወጣ ደንብ ወይም መመሪያ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረነ እና በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ እስካልተተካ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## 46. *ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን*

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ አገልግሎቱ ይህንን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ ተመስርቶ የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 47. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡
አዲስ አበባ---------------ቀን 2010 ዓ.ም

ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት